# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የጤና ሚኒስቴር

# የፌዴራል የጤና ሙያ ሥነ-ምግባር ኮሚቴ መመሪያ ቁጥር 878/2014

# ማውጫ

መግቢያ…………………………………………………………………………… 2

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ……………………………………………………………………3
2. ትርጓሜ………………………………………………………………………3
3. የተፈፃሚነት ወሰን…………………………………………………………….4
4. የመመሪያው አላማ……………………………………………………………4
5. መሠረታዊ መርሆች……………………………………………………………4

## ክፍል ሁለት

## የኮሚቴው ሃላፊነትና ተግባር እና አደረጃጀት

6. የኮሚቴው ተግባርና ኃላፊነት……………………………………………………… 6
7. የኮሚቴው አደረጃጀት……………………………………………………………7
8. የዋና ሰብሳቢ እና ምክትል ሰብሳቢ አመዳደብ………………………………………7
9. የዋና ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት……………………………………………8
10. የምክትል ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት………………………………………8
11. የኮሚቴው ፀሃፊ አመዳደብ…………………………………………………8
12. የፀሃፊ ተግባርና ኃላፊነት……………………………………………………8
13. የኮሚቴው አባላት ግዴታዎች………………………………………………8
14. በኮሚቴ አባልነት ለመመረጥ መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች…………………9
15. የኮሚቴ አባላት የስራ ዘመን…………………………………………………9
16. የኮሚቴ አባላት አመራረጥ…………………………………………………9
17. የኮሚቴው የመሰብሰቢያ ጊዜ………………………………………………10
18. ኮሚቴው የማይቀጥልባቸው ሁኔታዎች……………………………………10
19. ከአባልነት ስለማገድ ወይም ስለማሳናበት……………………………………11
20. ስለ ንዑስ ኮሚቴዎች…………………………………………………………11

## ክፍል ሦስት

## ስለ ቅሬታ አቀራረብ፣ ምርመራ እና የውሳኔ ሃሳብ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት

21. የቅሬታ አቀራረብ ሥነ ሥርዓት……………………………………………………..12
22. የቅድመ ማጣራት ሂደት…………………………………………………………..12
23. ክስን ስለመከላከል እና እንዲነሳ ስለመጠየቅ……………………………………..13
24. ቅሬታን ወይም የመከላከያ መልስን ስለማሻሻል…………………………………..14
25. ቅሬታን ስለማንሳት……………………………………………………………14
26. መጥሪያ ስለመላክ………………………………………………………………..14
27. ቅሬታን ስለመመርመር…………………………………………………………15
28. ጉዳዩ በሚታይበት እለት የቅሬታ አቅራቢው ወይም ቅሬታ የቀረበበት አካል መቅረት………………………………………………………………………………15
29. ስለ ምስክሮች……………………………………………………………………..16
30. ሌሎች ማሰረጃዎችን ስለመቀበልና ስለመመርመር………………………………..16
31. የውሳኔ ሃሳብ እና አፈጻጸም……………………………………………………16
32. አስተዳደራዊ እርምጃዎች……………………………………………………17
33. ቀላል አስተዳደራዊ እርምጃዎች………………………………………………18
34. ከባድ አስተዳደራዊ እርምጃዎች…………………………………………………..19
35. ይግባኝ……………………………………………………………………………..20
36.ተፈጻሚነት የሌላቸው ህጎች……………………………………………………20
37.መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ………………………………………………..……..20

# መግቢያ

የጤና ሙያ ስነ-ምግባር ኮሚቴ ከጤና ባለሙያዎች የሙያ ብቃት ማነስ እና የስነ - ምግባር ጉድለት እና ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚቀርቡ ቅሬታዎች ምርመራ እና የውሳኔ ሀሳብ አሰጣጥ ሂደትን በሕግ እና ሥርዓት መምራት በማስፈለጉ፤

የጤና ሙያ ሥነ ምግባር ኮሚቴውን ዝርዝር አሰራር፣ ተግባርና ኃላፊነት በሕግ በመወሰን የአሰራር ሂደቱ ግልጽነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት እንዲሆን ማድረግ በማስፈለጉ፤

የጤና ሙያ ስነ ምግባር ኮሚቴን አሰራር ግልጽነትና ተጠያቂነትን በማስፈን የሕክምና ቅሬታ አቅራቢዎች ቀልጣፋ እና ፍትሃዊ ውሳኔ እንዲያገኙ እንዲሁም የሕክምና አገልግሎት አሰጣጥ ጥራትን ማረጋገጥ በማስፈለጉ፤

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጤና ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 1112/2011 አንቀጽ 71 ንዑስ አንቀጽ 2 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "የፌዴራል የጤና ሙያ ሥነ ምግባር ኮሚቴ መመሪያ ቁጥር 878/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

   1) "ኮሚቴ" ማለት በጤና ሚኒስቴር ስር የሚገኘው የጤና ሙያ ስነ-ምግባር ኮሚቴ ነው፤
   2) "የጤና ሙያ ስነ-ምግባር ኮሚቴ" ማለት በጤና አገልግሎት ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን በመቀበል እና በመመርመር ሙያዊ የውሳኔ ሃሳብ ለሚኒስቴሩ የበላይ ኃላፊ የሚያቀርብ አካል ነው፤
   3) "የጤና ባለሙያ" ማለት እውቅና ከተሰጠው የትምህርት ተቋም በጤና የትምህርት ዘርፍ የሰለጠነ እና የጤና አገልግሎት ለመስጠት በአስፈጻሚ አካል የተመዘገበ ሰዉ ነዉ፤
   4) "የጤና ተቋም" ማለት ማንኛውም የጤና አገልግሎት ለመስጠት በአስፈጻሚ አካል የተመዘገበ ተቋም ሆኖ ለድርጅቶች የውስጥ ሰራተኞቻቸው የጤና አገልግሎት የሚሰጡ ጤና ተቋማትንም ይጨምራል፤
   5) "ቅሬታ" ማለት ከጤና አገልግሎት አሰጣጥ እና የባለሙያ የስነ ምግባር ጉድለት ጋር ተያይዞ ለኮሚቴው በጽሁፍ የሚቀርብ የቅሬታ አቤቱታ ነው፤
   6) "ቅሬታ አቅራቢ" ማለት በጤና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሕክምና ቅሬታ አቤቱታ የሚያቀርብ ሰው ነው፤
   7) "ቅሬታ የቀረበበት ሰው" ማለት የቅሬታ አቤቱታ የቀረበበት የጤና ባለሙያ ወይም የጤና ተቋም ነው፤
   8) "የጤና አገልግሎት" ማለት በጤና ተቋማት የሚሰጥ የጤና ማበልጸግ፣ በሽታ የመከላከል፣ የማከም እና የማገገም አገልግሎት ነዉ፤
   9) "የጤና ሙያ ፈቃድ" ማለት የጤና አገልግሎት ወይም ተደጋጋፊ ወይም አማራጭ የሕክምና አገልግሎት ለሚሰጥ ባለሙያ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው፤

10) “አስፈጻሚ አካል” ማለት የጤና አገልግሎት እና የጤና ባለሙያዎችን የመቆጣጠር ስልጣን አግባብነት ባለው ሕግ የተሰጠው አካል ነው፤

11) “ተቆጣጣሪ” ማለት የጤና ቁጥጥር ተግባራትን እንዲያከናውን በአስፈጻሚ አካላት ውስጥ የተመደበ ባለሙያ ነው፤

12) “ሚኒስቴር” ማለት የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የጤና ሚኒስቴር ነው፤

13) “ሚኒስትር” ማለት የጤና  ሚኒስትር ነው፤

14) “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

15) ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው አገላለጽ ሴትንም ይጨምራል፡፡

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ የፌዴራል መንግስት እና የጤና ሙያ ስነ ምግባር ኮሚቴ የሌላቸው ክልሎች በሚያስተዳድሯቸው የጤና አገልግሎት በሚሰጡ ጤና ተቋማት እና የጤና ባለሙያዎች ላይ በሚቀርብ የጤና አገልግሎት ቅሬታ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

4. <u>ዓላማ</u>

የኮሚቴውን የአሰራር ሂደት በሕግ ማእቀፍ እንዲመራ በማድረግ አሰራሩን ግልጽና ፍትሃዊ በማድረግ ቀልጣፋ እና ፍትሃዊ የቅሬታ አፈታት ስርዓትን ለመዘርጋት ነው፡፡

5. <u>መሰረታዊ መርሆች</u>

1) የሥነ ምግባር ኮሚቴው በማንኛውም ጊዜ የጤና አገልግሎት ተጠቃሚውን የማህበረሰብ ክፍል መብትና ጥቅም ማስከበር አለበት፡፡
2) የሥነ ምግባር ኮሚቴው የሚከተላቸው የአሰራር ሂደቶች እና የሚሰጣቸው ሙያዊ የውሳኔ ሃሳቦች አግባብነት ያላቸው ሕጎችንና የሙያ መርሆዎችን የተከተለ መሆን አለበት፡፡

## ክፍል ሁለት

## የኮሚቴው ተግባር ሃላፊነት እና አደረጃጀት

### 6. የኮሚቴው ተግባርና ኃላፊነት

ኮሚቴው የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1) በጤና ባለሙያዎች የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚቀርብ የጤና አገልግሎት እና የስነምግባር ቅሬታ ይቀበላል፣ይመረምራል፣መንስኤዎቻቸውን አጣርቶ ለሚኒስቴሩ የውሳኔ ሀሳብ የማቅረብ፤
2) አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከሚኒስቴሩ ጋር በመመካከር ነጻ የሆነ አጣሪ ወይም መርማሪ አካል በመመደብ የቀረበው ቅሬታ እንዲጣራ የማድረግ፤
3) የቅሬታ አቤቱታ ባይቀርብም የጤና ባለሙያዎችን የስነ ምግባር ጥሰት በተመለከተ ጥቆማ ሲደርሰው ወይም መረጃ ሲያገኝ የማጣራት፤
4) ተግባርና ኃላፊነቱን በአግባቡ ይወጣ ዘንድ ንዑስ ኮሚቴዎችን ማቋቋም፤
5) ቅሬታ በቀረበበት ባለሙያ ላይ ጉዳዩ ተጣርቶ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ የሙያ ስራ ፈቃዱ እንዲታገድ ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ፤
6) የስነ ምግባር ግድፈት የፈጸመን ባለሙያ የሙያ ስራ ፈቃድ ማገድን እና መሰረዘን ጨምሮ በዚህ መመሪያ መሰረት የተቀመጡ አግባብነት ያላቸው ሌሎች እርምጃዎች መውሰድ፤
7) በተደጋጋሚ በጤና አገልግሎት አሰጣጥ እና በባለሙያዎች የስነ ምግባር ጉድለት ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎች መንስዔዎችን ይለያል፤ እነዚህን ችግሮች ዘላቂ በሆነ መንገድ ለመፍታት እንዲቻል የፖሊሲ ሀሳቦችን ማመንጨት እና ለሚኒስቴሩ የማቅረብ፤
8) በቀረበለት ቅሬታ ላይ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዲታገድ ለሚኒስቴሩ የውሳኔ ሀሳብ ማቅረብ፤
9) የቀረበለትን ቅሬታ ለማየት በቂ ማስረጃ መኖሩን ሲያረጋግጥ ቅሬታ የቀረበበት የጤና ባለሙያ ወይም ተቋም መልሱን በሰላሳ ቀን ውስጥ እንዲያቀርብ መጥሪያ የመላክ፤
10) ሚኒስቴሩ በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት ሌሎች ተግባራትን የማከናወን፡፡

## 7. <u>የኮሚቴው አደረጃጀት</u>

ኮሚቴው፡-

1) ዋና ሰብሳቢ፤
2) ምክትል ሰብሳቢ
3) ፀኃፊ፤ እና
4) አስፈላጊ የኮሚቴ አባላት ይኖሩታል።

## 8. <u>የዋና ሰብሳቢ እና ምክትል ሰብሳቢ አመዳደብ</u>

1) ሚኒስቴሩ ከኮሚቴ አባላት መካከል አንድ ዋና ሰብሳቢ ይመርጣል።
2) ምክትል ሰብሳቢ በመጀመሪያው የኮሚቴው ስብሰባ እለት በኮሚቴ አባላት ይመረጣል።
3) ዋና ሰብሳቢው እና ምክትል ሰብሳቢው በማይኖሩበት ጊዜ የሰብሳቢነት ስልጣንና ኃላፊነት የሚወጣ ጊዜያዊ ሰብሳቢ ከኮሚቴ አባላት ውስጥ ሊመረጥ ይችላል።

## 9. <u>የዋና ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት</u>

የኮሚቴው ዋና ሰብሳቢ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1) የኮሚቴውን የስብሰባ አጀንዳ ይወስናል፤ ያቀርባል፤
2) የኮሚቴውን ስብሰባ በበላይነት ይመራል፤
3) የኮሚቴው አባላት በዚህ መመሪያ እና ሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች እና የአሰራር መርሆዎች መሰረት ኃላፊነታቸውን እየተወጡ መሆኑን ይከታተላል፤
4) ማንኛውም የኮሚቴ አባል የስነ ምግባር ግድፈት አለበት ብሎ ሲያምን ለሚኒስቴሩ የበላይ ኃላፊ ያሳውቃል፡-
5) የሚቀርቡ ቅሬታዎችን እና የኮሚቴውን ስራ በተመለከተ ከሚኒስቴሩ የበላይ ኃላፊ ጋር መረጃ ይለዋወጣል፤
6) ኮሚቴው ያስተላለፈውን የመጨረሻ የውሳኔ ሃሳብ ለሚኒስቴሩ የበላይ ኃላፊ በጽሁፍ ያሳውቃል፤
7) በሚኒስቴሩ እና በኮሚቴው የሚሰጡ ሌሎች ኃላፊነቶችን ይፈጽማል፡፡

## 10. የምክትል ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት

ዋና ሰብሳቢው በማይኖርበት ጊዜ ዋና ሰብሳቢውን ተክቶ ተግባርና ኃላፊነቱን ይወጣል፡፡

## 11. የኮሚቴው ፀሃፊ አመዳደብ

ሚኒስቴሩ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 12 የተዘረዘሩትን ተግባርና ኃላፊነቶች የሚወጣ አንድ የሕግ ባለሙያ ይመድባል።

## 12. የፀሃፊ ተግባርና ኃላፊነት

የኮሚቴው ፀኃፊ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1) የቅሬታ አቤቱታዎችንና ተያያዥ ሠነዶችን ይቀበላል፣ በአግባቡ ይይዛል፣ ለኮሚቴው ያቀርባል፤
2) የኮሚቴውን ስብሰባ ቃለ ጉባዔ ይይዛል፤
3) በቀረበው የቅሬታ ማመልከቻ ላይ ያልተሟላ ማስረጃ ካለ እንደአስፈላጊነቱ ይሰበስባል፣ እንዲሟሉ ወይም እንዲቀርቡ ያደርጋል፤
4) የኮሚቴውን የስብሰባ ጊዜ ለኮሚቴ አባላት እና ለሚመለከታቸው አካላት ያሳውቃል፤
5) የስብሳባ አጀንዳዎችን፣ ቀን እና ተያያዥ ጉዳዮችን በተመለከተ ለዋና ሰብሳቢው የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፤
6) በቃለ ጉባዔ የተያዘ የኮሚቴውን የውሳኔ ሃሳብ በጽሁፍ በማዘጋጀት ለኮሚቴው እና ለሚኒስቴሩ የበላይ ኃላፊ ያቀርባል፤
7) የኮሚቴውን የውሳኔ ሃሳብ የሚያስቀይር ወይም በውሳኔ ሃሳቡ ላይ ተጽእኖ ሊኖረው የሚችል እውነታ ወይም ማስረጃ አለ ብሎ ሲያምን ለኮሚቴው ወይም ለዋና ሰብሳቢው ያሳውቃል፤
8) ሌሎች በሚኒስቴሩ እና በኮሚቴው የሚሰጡትን ተግባርና ኃላፊነቶች ይፈጽማል፡፡

## 13. የኮሚቴ አባላት ግዴታዎች

ማንኛውም የሥነ ምግባር ኮሚቴ አባል፡-

1) ማንኛውም የሥነ ምግባር ኮሚቴ አባል የሙያ ሥነ ምግባሩን የመጠበቅ፤

2) የስነ ምግባር ግድፈት በኮሚቴ አባል ተፈጽሟል ብሎ ያመነ ማንኛውም የኮሚቴ አባል ይሄንኑ ለዋና ሰብሳቢው የማሳወቅ፤
3) በአቢይ እና ንዑስ ኮሚቴ ስብሰባዎች ላይ አዘውትሮ መገኘት፤
4) በማጣራት ሒደት በእጃቸው የሚገኝ ልዩ ልዩ ሰነዶችን በጥንቃቄና በሚስጥር መያዝ፤እና
5) በሚቀርብ ጉዳይ ላይ የጥቅም ግጭት አለ ብሎ ሲያምን ለኮሚቴው አሳውቆ ከማጣራት ሂደት ራስን የማግለል ግዴታ አለበት፡፡

## 14. በኮሚቴ አባልነት ለመመረጥ መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች

የኮሚቴ አባል ከሚወክለው አካል በፅሁፍ በተረጋገጠ ደብዳቤ አማካይነት የሚሰየም ሲሆን በኮሚቴ አባልነት ለመመረጥ የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላት አለባቸው፡-

1) የጤና ባለሙያ ከሆነ ሕጋዊ የሙያ የስራ ፈቃድ ያለው፤
2) ጥሩ ስነ ምግባር ያለው፤
3) በስራው ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር ከሚችል ሱስ ነጻ የሆነ፤
4) በሕግ መብቱ ያልተገደበ፤
5) ከሙያ ጋር በተያያዘ ወይም ለህሊና ተጻራሪ በሆነ ወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ ያልተባለ፤
6) ሕዝብን በቅንነት ለማገልገል ፍላጎት ያለው፤

መሆን አለበት፡፡

## 15. የኮሚቴ አባላት የስራ ዘመን

1) የማንኛውም የኮሚቴው ሰብሳቢ፣ ጸሃፊ እና አባል የስራ ዘመን ከተመረጠበት ጊዜ ጀምሮ ከሶስት ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ ነው፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት በኮሚቴ አባልነት ያገለገለ ሰው ከሁለት የአገልግሎት የስራ ዘመን በላይ መመረጥ አይችልም፡፡

## 16. የኮሚቴ አባላት አመራረጥ

የኮሚቴ አባላት አመራረጥና የሙያ ስብጥር ከ፡-

1) ኢትዮጵያ የአጥንት ህክምና ማህበር፤
2) ጤና ሚኒስቴር የሕክምና አገልግሎት ዳይሬክቶሬት፤
3) የኢትዮጵያ የፋርማሲ ማህበር፤

4) የኢትዮጵያ የቀዶ ህክምና ማህበር፤

5) የኢትዮጵያ የፅንስና ማህፀን ሃኪሞች ማህበር፤

6) የኢትዮጵያ ህክምና ማህበር፤

7) የኢትዮጵያ የውስጥ ደዌ ህክምና ማህበር፤

8) የኢትዮጵያ ሜዲካል ላብራቶሪ ማህበር፤

9) የኢትዮጵያ ራዲዮሎጂስቶችና ራዲዮግራፈሮች ማህበር፤

10) ጤና ሚኒስቴር የጤናና ጤና ነክ ተቋማት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት፤

11) የኢትዮጵያ ነርሶች ማህበር፤

12) የኢትዮጵያ ሚድዋይፎች ማህበር፤

13) የኢትዮጵያ ጤና አጠባበቅ ማህበር፤

14) የኢትዮጵያ አንስቴቲስቶች ማህበር እና አግባብነት ካላቸው ሌሎች አካላት፤

15) ጤና ሚኒስቴር እናቶችና ሕጻናት ጤና ዳይሬክቶሬት፤ጤነናና ጤና ነክ ተቋማት ቁጥጥር ዳይሬቶሬት፣ የጤና ባለሞያዎች ምዘናና ፍቃድ ዳይሬክቶሬት፤

16) ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሁለት አባላት

17)ጤና ሚኒስቴር የሕግ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት የተውጣጡ አባላትን ያካተተ መሆን አለበት፡፡

## 17. <u>የኮሚቴው የመሰብሰቢያ ጊዜ</u>

1) የጤና ሙያ የስነ-ምግባር ኮሚቴ በወር አራት??? ጊዜ በመደበኛነት ይሰበስባል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ስር የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚቴው እንደ አስፈላጊነቱ ንዑሳን ኮሚቴዎችን ጨምሮ በማንኛውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፡፡

## 18. <u>ኮሚቴው የማይቀጥልባቸው ሁኔታዎች</u>

1) ኮሚቴው የተጣለበትን ተግባርና ኃላፊነት አልተወጣም ብሎ ሚኒስቴሩ ሲያምን አስፈላጊውን የማጣራት ስራ እንዲያከናውን ገለልተኛ አካል ሊሰይም ይችላል።

2) ኮሚቴው በዚህ መመሪያ የተቀመጠውን ተግባርና ኃላፊነት በአግባቡ አልተወጣም ብሎ ሲያምን ሚኒስቴሩ ኮሚቴውን ሊያፈርሰው ይችላል፡፡

## 19. ከአባልነት ስለማገድ ወይም ስለማሰናበት

ማንኛውም የኮሚቴው አባል በሚከተሉት ምክንያቶች ከአባልነት ሊታገድ ይችላል፡-

1) የሙያ ስነ ምግባር ግድፈት ሲፈፅም ብሎም በማስረጃ ሲጋገጥ፤
2) በዚህ መመሪያ ውስጥ የተቀመጡ ተግባርና ኃላፊነቶችን እንዳይወጣ የሚያደርግ የአካል ወይም የአእምሮ ጤና እክል የገጠመው ከሆነ፤
3) በስርቆት፣ ማጭበርበር፣ ሙስና፣ በእምነት ማጉደል እና መሰል በወራዳነት ተግባር የሚፈጸሙ ወንጀሎች ተከስሶ በፍርድ ቤት ጥፋተኛ ከተባለ፤
4) በበጀት ዓመቱ በተከታታይ ሶስት ስብሰባዎችን ወይም ኮሚቴው ካካሄዳቸው ጠቅላላ ስብሰባዎች ውስጥ ስድስት ስብሰባዎችን ያለበቂ ምክንያት የቀረ እንደሆነ፤
5) ከኮሚቴ አባልነት ለመልቀቅ በራሱ ፍላጎት ያመለከተና ሚኒስቴሩ ከፈቀደ፤
6) የኮሚቴውን አሰራር እና መልካም ስም ሊያጎድፍ የሚችል ወይም የግል ፍላጎቱን የሚያንጸባርቅ ከሆነ፤
7) ኮሚቴው የተጣለበትን ኃላፊነት እንዳይወጣ እንቅፋት ሆኗል ብሎ ኮሚቴው ካመነ
8) የኮሚቴውን አባል የወከለው አካል እንዲነሳለት በፅሁፍ ጥያቄ ሲያቀርብ

## 20. ስለ ንዑስ ኮሚቴዎች

1) ንዑስ ኮሚቴው ዋናው ኮሚቴ በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት ስራውን ያከናውናል፡፡
2) በዚህ መመሪያ መሰረት በኮሚቴው የተቋቋመ ንዑስ ኮሚቴ በንዑስ ኮሚቴ አባላቱ የሚሰየሙ የራሱ ሰብሳቢ እና ጸሃፊ ይኖረዋል።
3) ንዑስ ኮሚቴው፡-

   ሀ) በተዘጋጀው ቅጽ መሰረት ለተከሳሽ ወይም ቅሬታ ለቀረበበት አካል መጥሪያ ይጽፋል፤

   ለ) ከጤና ተቆጣጣሪው ጋር በመሆን ለማስረጃነት አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን ወይም ሌሎች ማስረጃዎችን ይፈትሻል፣ ይይዛል፤ እና

   ሐ) ከጉዳዩ ጋር ተያያዥ የሆኑ ሌሎች ተግባራትን ይፈጽማል

## ክፍል ሶስት

## ስለ ቅሬታ አቀራረብ፣ ምርመራ እና የውሳኔ ሃሳብ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት

### 21. የቅሬታ አቀራረብ ሥነ ሥርዓት

1) ቅሬታ ሊቀርብ የሚችለው ጉዳት በደረሰበት ግለሰብ፣ በአሳዳጊው፣ በሕጋዊ ተወካዩ ወይም ጉዳዩ ይመለከተኛል በሚል አካል ሊሆን ይችላል፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚቀርብ ቅሬታ ጉዳዩ በታወቀ በአንድ ዓመት ውስጥ ወይም ሌላ አሳማኝ ምክንያት በሚኖርበት ጊዜ ውስጥ በሁለት ዓመት ውስጥ ለኮሚቴው ጸሃፊ መቅረብ አለበት፡፡
3) ቅሬታ ሊቀርብ የሚችለው በጽሁፍ ሆኖ የቅሬታውን ዝርዝር ሁኔታ፣ በባለሙያው ተፈጸመ የተባለው ግድፈት፣ የባለሙያው ሙሉ ስምና አድራሻ እና የቅሬታ አቅራቢውን ፊርማ የያዘ መሆን አለበት፡፡
4) ቅሬታ አቅራቢው በኮሚቴው ጸሃፊ የሚቀርብለትን ቅጽ በአግባቡ መሙላት አለበት፡፡
5) ቅሬታ አቅራቢው የመታወቂያ ደብተሩን ኮፒ በአባሪነት ማያያዝ አለበት፡፡
6) ቅሬታ አቅራቢው ምስክሮች ወይም ቅሬታውን የሚያጠናክሩለት ማስረጃዎች ካሉት የምስክሮችን ስም ዝርዝር እና አድራሻ እንዲሁም የማስረጃ ሰነዱን ከቅሬታ ማመልከቻው ጋር አያይዞ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
7) የኮሚቴው ጸሃፊ ቅሬታ ለቀረበበት ሰው የቀረበበትን የቅሬታ ዝርዝር ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

### 22. የቅድመ ማጣራት ሂደት

1) ኮሚቴው በዚህ መመሪያ መሰረት በቀረበ ቅሬታ ላይ የማጣራት ስራ ለማካሄድ የቀረበው ማስረጃ በቂ ሆኖ ካላገኘው ከተከሳሽ ወይም ከሌላ ማንኛውም አካል ማስረጃ እንዲሰበሰብ ያደርጋል፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት በሚሰበሰብ ማስረጃ መሰረት ግድፈት ተፈጽሟል የሚያስብል ምክንያት ከተገኘ ኮሚቴው ጥልቅ ምርመራ ያካሂዳል፡፡
3) ኮሚቴው የመጨረሻውን የውሳኔ ሃሳብ ከመስጠቱ በፊት የቀረበለትን የቅሬታ አቤቱታ ወይም የጉዳዩን ባህሪ መሰረት በማድረግ ባለሙያው የጤና አገልግሎት እንዳይሰጥ የሙያ ፈቃዱ በጊዜአዊነት እንዲታገድ ሊያደርግ ወይም የተወሰኑ

የሙያ ተግባራትን ብቻ እንዲያከናውን ትእዛዝ ሊሰጥ ወይም ይህንን ለሚመለከተው አካል ሊያሳውቅ ይችላል፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሰረት የተላለፈው የእግድ ወይም የክልከላ ትእዛዝ ከተላለፈበት ቀን ጀምሮ ከ90 ቀናት መብለጥ የለበትም።

5) አቤቱታ የቀረበበት ባለሙያ ላይ ኮሚቴው ምንም አይነት አሳማኝ ማስረጃ ካላገኘበት እገዳውን ወይም ክልከላውን ወዲያውኑ ማንሳት አለበት፡፡

## 23. ክስን ስለመከላከል እና እንዲነሳ ስለመጠየቅ

1) ቅሬታ እንደቀረበበት ያወቀ እና ቀርቦ እንዲከላከል በኮሚቴው ጸሃፊ በኩል መልእክት የተላለፈለት ባለሙያ መጥሪያው በደረሰው በ10 ተከታታይ ቀናት ውስጥ እንደሁኔታው ምስክሮች እና ማስረጃዎች ካሉት ይህንኑ በማካተት የመከላከያ መልሱን ማቅረብ አለበት፡፡

2) የቀረበው የመከላከያ መልስ በዋናነት የቅሬታ አቅራቢውንና ቅሬታ የቀረበበትን ሰው ስምና ሙሉ አድራሻ፣ ለእያንዳንዱ የክስ ዝርዝር የቀረበ የመከላከያ መልስ ሙሉ መግለጫ እንዲሁም እንደሁኔታው የምስክሮችን ሙሉ ስምና አድራሻ እና የማስረጃ ሰነዶችን ኮፒ ማያያዝ አለበት፡፡

3) ተከሳሽ ያቀረበውን የመከላከያ መልስ ኮፒ ቅሬታ አቅራቢው እንዲወስድ የኮሚቴው ጸሃፊ ለቅሬታ አቅራቢው ይነግራል፡፡

4) ቅሬታ የቀረበበት ባለሙያ በቀረበበበት እያንዳንዱ የክስ ፍሬ ነገር ላይ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የመከላከያ መልስ ካላቀረበ መከላከያ መልስ ያልቀረበበት ፍሬ ነገርን በሚመለከት እንዳልተከላከለ ተቆጥሮ ክሱን እንደተቀበለው ይቆጠራል፡፡

5) ቅሬታ የቀረበበት ባለሙያ በቀረበው ክስ መሰረት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማቅረብ ክሱ እንዲነሳለት መጠየቅ የሚችለው የቀረበው ክስ፡-

ሀ) በዚህ መመሪያ መሰረት ለኮሚቴው ከተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት ውጭ ከሆነ፤

ለ) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 15 (2) መሰረት የጊዜ ገደቡ ያለፈ ከሆነ፤ ወይም

ሐ) ከዚህ በፊት በኮሚቴው የተነሳለት ከሆነ ወይም የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠበት ከሆነ ነው፡፡

6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) መሰረት መጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ከቀረበ ኮሚቴው የክሱን ፍሬ ነገር ከመመልከቱ በፊት በቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃዎሚያ ላይ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡
7) ኮሚቴው የክሱን ፍሬ ነገር መመልከት ከጀመረ በኋላ የሚቀርብ ማንኛውም አይነት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ተቀባይነት የለውም፡፡

## 24. ቅሬታን ወይም የመከላከያ መልስን ስለማሻሻል

1) የቅሬታ አቤቱታን ወይም የመከላከያ መልስ ሊሻሻል የሚችለው በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት እና አግባብነቱ በኮሚቴው ታይቶ ከታመነበት ብቻ ነው፡፡
2) ኮሚቴው የቀረበው የቅሬታ ማመልከቻ ወይም የመከላከያ መልስ መሻሻል አለበት ብሎ ሲያምን ይኸው እንዲሻሻል በማንኛውም ጊዜ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡
3) የቀረበው የቅሬታ ማመልከቻ ወይም የመከላከያ መልስ በዚህ አንቀጽ መሰረት ከተሻሻለ አንደኛው ተከራከሪ ወገን እንደሁኔታው ሊያሻሻል ይችላል፡፡

## 25. ቅሬታን ስለማንሳት

1) ቅሬታ አቅራቢው ቅሬታውን ማንሳት የሚችለው፡-
   ሀ) ይኸው ጥያቄ በጽሁፍ ከቀረበ፤
   ለ) ጉዳዩ የማህበረሰቡን ጥቅም የማይጎዳ መሆኑ በኮሚቴው ከታመነ፤
   ሐ) ጥያቄው የቀረበው ኮሚቴው የመጨረሻ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ከሆነ፤
   ብቻ ነው፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የተነሳ ማንኛውም ቅሬታ በድጋሚ ለኮሚቴው ሊቀርብ አይችልም፡፡

## 26. መጥሪያ ስለመላክ

1) ኮሚቴው ጉዳዩን ለመስማት ከቀጠረበት አስር ቀናት በፊት የኮሚቴው ጸሃፊ የቅሬታውን ኮፒ ቅሬታ ለቀረበበት ባለሙያ እንዲደርሰው ማድረግ አለበት፡
2) የቅሬታ ኮፒው ለባለሙያው በቀጥታ ሊሰጥ፣ ወይም ባሙያው መጥቶ እንዲወስድ ወይም ባለሙያው ካልተገኘ ለሚሰራበት ተቋም ሊሰጥ ይችላል፡፡

3) ቅሬታውን ያቀረበው አካል ወይም ቅሬታ የቀረበበት ባለሙያ ጉዳዩ በሚሰማበት ጊዜ እንዲገኝ አስፈላጊ ነው ብሎ ኮሚቴው ካመነ በጸሃፊው አማካኝነት የስብሰባው ቀን፣ ሰዓትና ቦታን በመጥቀስ እንዲቀርብ ጥሪ ይደረግለታል፡፡

27. <u>ቅሬታን ስለመመርመር</u>

1) ኮሚቴው የመከላከያ መልስ ከደረሰው በኋላ ጉዳዩን ለማየት ይሰበሰባል፡፡
2) ኮሚቴው መብራራት አለበት ብሎ ያመነው ነገር ካለ የመጨረሻ ውሳኔ ከማስተላለፉ በፊት ጉዳየዩን ግልጽ ማድረግ ይኖርበታል፡፡
3) ኮሚቴው የቀረበውን አቤቱታ፣ የመከላከያ መልስ እና ማስረጃዎች ካየ በኋላ ውሳኔ ያስተላልፋል፡፡
4) በቅሬታ ማመልከቻው ላይ ከቀረበው የየክስ ዝርዝር በተጨማሪ ኮሚቴው ሌላ ተያያዥ የስነ ምግባር ግድፈት አለ ብሎ ካመነ በመጀመሪያ በቀረቡት የክስ ዝርዝሮች ላይ በመጨጨመር ጉዳዩ እንዲጣራ እና መከላከያ መልስ እንዲሰጥበት ሊያደርግ ይችላል፡፡

28. <u>ጉዳዩ በሚታይበት እለት የቅረታ አቅራቢው ወይም ቅሬተ የቀረበበት አካል መቅረት</u>

1) ቅሬታ የቀረበበት ጉዳዩ በሚታይበት ጊዜ እንዲቀርብ በኮሚቴው ተጠርቶ ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ ኮሚቴው የቅሬታ አቅራቢውን ማስረጃዎች እና የምስክር ቃል ሰምቶ በተሰጠው ማስረጃ መሰረት የውሳኔ ሃሳብ ማስተላለፍ ይችላል፡፡
2) ጉዳዩ በሚታይበት ጊዜ መገኘት እንዳለበት የተነገረው ቅሬታ የቀረበበት ሳይገኝ የቀረበትን አሳማኝ ምክንያት በአስር ቀናት ውስጥ ለኮሚቴው ጸሃፊ ካቀረበ እና ኮሚቴው ካመነበት እንደገና ሊታይ ይችላል፡፡
3) ቅሬታ አቅራቢው ጉዳዩ በሚታይበት ጊዜ ላይ መገኘት እንዳለበት ተነግሮት ሳይቀርብ ሲቀር ጉዳዩ የማህበረሰቡን ጥቅም የማይጎዳ ከሆነ ኮሚቴው የቀረበው ቅሬታ ውድቅ እንዲሆን ሊወስን ይችላል፡፡
4) ጉዳዩ በሚታይበት ጊዜ ላይ መገኘት እንዳለበት የተነገረው ቅሬታ አቅራቢ ሳይገኝ ቀርቶ የቀረበትን አሳማኝ ምክንያት ከቀረበት አስር ቀናት ውስጥ ለኮሚቴው ጸሃፊ እና ኮሚቴው ካመነበት እንደገና ሊታይ ይችላል፡፡

## 29. <u>ስለ ምስክሮች</u>

1) ኮሚቴው በቀረበው ክስ ላይ ምስክሮች የምስክርነት ቃላቸውን እንዲሰጡ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ጥሪ ያደርጋል፡፡
2) በተመሳሳይ ወይም ተያያዥ በሆኑ ጉዳዮች ላይ በአንድ ቀንና ሰአት እንዲቀርቡ የተጠየቁ ምስክሮች ምስክርነታቸውን ለየብቻቸው እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡
3) ቅሬታ አቅራቢ ወይም ተከሳሽ ለምስክርነት ያቀረበውን ሰው እንዲቀርብ ለማድረግ የኮሚቴውን መጥሪያ የሚያደርሰው እነዚሁን ምስክሮች የጠራቸው ወገን ነው፡፡
4) መጥሪያ አልቀበልም ያለ ወይም መጥሪያ ደርሶት ሳይቀርብ የቀረ ምስክር አግባብ ባለው የሕግ አካል ተገዶ ምስክርነቱን እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡
5) የምስክርነት ቃል እንዲሰጥ የተጠራ ምስክር የሚሰጠው የምስክርነት ቃል በጽሁፍ መስፈር እና መፈረም አለበት፡፡
6) ጉዳዩ በሚታይበት ጊዜ ቅሬታ አቅራቢ ወይም ቅሬታ የቀረበበት በኮሚቴው ከተጠራ ለምስክሩ መስቀለኛ ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

## 30. <u>ሌሎች ማሰረጃዎችን ስለመቀበልና ስለመመርመር</u>

1) ኮሚቴው ለጉዳዩ አስፈላጊ ነው ብሎ ያመነበትን ማንኛውንም ማስረጃ ሊቀበል ይችላል፡፡
2) ኮሚቴው ውሳኔ ለማስተላለፍ ተጨማሪ ማረጋገጫ እና ምስክር ያስፈልጋል ብሎ ካመነ ተጨማሪ ማረጋገጫ እና ምስክር እንዲቀርብ ሊያዝ ይችላል፡፡
3) የጤና መረጃን፣የሕክምና መሳሪያ ወይም ሌሎች ተያያዥ ማስረጃዎችን የሚይዝ ማንኛውም የጤና ተቋም ኮሚቴው ከሚኒስቴሩ በሚወክለው አካል ጉዳዩን ለማጣራት አስፈላጊውን ምርመራ እንዲያደርግ መፍቀድ ይኖርበታል፡፡

## 31. <u>የውሳኔ ሃሳብ እና አፈጻጸም</u>

1) ኮሚቴው የመስማት ሂደቱን ካጠናቀቀ በኋላ ቢያንስ በሚቀጥለው የስብሰባ ጊዜ የውሳኔ ሃሳብ ማሳለፍ አለበት፡፡
2) የመጨረሻ የውሳኔ ሃሳብ በተሰጠ በአስራ አምስት ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ የኮሚቴው ጸሃፊ ውሳኔዎችን በጽሁፍ አዘጋጅቶ ወዲያውኑ እንዲፈረም ያቀርባል፡፡

3) የኮሚቴው የውሳኔ ሃሳብ በተፈረመ በሶስት ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ ለሚኒስቴሩ የበላይ ኃላፊ መቅረብ አለበት፡፡

4) የውሳኔ ሃሳቡ በሚኒስቴሩ የበላይ ኃላፊ ከጸደቀ በኋላ እንደሁኔታው ውሳኔው **ቅሬታ በቀረበበት**፣ በቀጣሪው ተቋም፣ በፍቃድ ሰጭ አካል ወይም ሌሎች አግባብነት ባላቸው አካላት እንዲፈጸም ይደረጋል፡፡

5) ውሳኔው በዚህ መመሪያ መሰረት ይግባኝ ካልተባለበት በስተቀር **ቅሬታ በቀረበበት** አካል ተቀባይነት ሳያገኝ ከቀረ ወይም ተፈጻሚ ካልሆነ ሚኒስቴሩ እንደሁኔታው አስተዳደራዊ እርምጃ መውሰድ ወይም ጉዳዩን አግባብ ላለው የሕግ አስፈጻሚ አካል ማስተላለፍ ይችላል፡፡

## 32. <u>አስተዳደራዊ እርምጃዎች</u>

1) የተፈጸመውን የስነ ምግባር ግድፈት ክብደት መሰረት በማድረግ ኮሚቴው ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት አንዱን ወይም ከዚያ በላይ የሆነ እርምጃ እንዲወሰድ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፡-

   ሀ) የቃል ማስጠንቀቂያ መስጠት፤

   ለ) የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት፤

   ሐ) ስልጠና ወይም ትምህርት እንዲወስድ ማድረግ፤

   መ) ልምድ ባለው ባለሙያ ክትትል ስር ሆኖ ለተወሰነ ጊዜ እንዲሰራ ማድረግ፤

   ሠ) ጥፋተኛ ከተባለበት ጉዳይ ጋር ተያያዥ የሆኑ የሙያ ስራዎችን እንዳይሰራ ማገድ፤

   ረ) የሙያ ስራ ፈቃዱን ለተወሰነ ጊዜ ማገድ፤

   ሰ) የሙያ ስራ ፈቃዱን መሰረዝ፤ ወይም

   ሸ) አግባብነት ያላቸው ሌሎች እርምጃዎች፤

2) በጉዳዩ ላይ ባለሙያው የሚሰራበት የጤና ተቋም ለስነ ምግባር ግድፈቱ አስተዋጽኦ ካለው ኮሚቴው ይኼንኑ ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ ማሳወቅ እና አግባብ ያለው እርምጃ እንዲወሰድ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ስር ከተራ ቁጥር "ሀ" እስከ "መ" የተዘረዘሩት ቀላል አስተዳደራዊ እርምጃዎች ተብለው ይመደባሉ፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ስር ከተራ ቁጥር "ሠ" እስከ "ሰ" የተዘረዘሩት ከባድ አስተዳደራዊ እርምጃዎች ተብለው ይመደባሉ፡፡

5) ኮሚቴው ቅሬታ የቀረበበት የስነ ምግባር ግድፈት ክብደት፣ ባህሪ፣ በጤና ላይ ያደረሰውን ጉዳት እና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ጉዳዮች ከግምት ውስጥ በማስገባት በቀላል ወይም በከባድ አስተዳደራዊ እርምጃ ቅጣት ይወስናል፡፡

6) በዚህ አንቀጽ መሰረት ከባድ አስተዳደራዊ እርምጃ የሚወሰደው የተፈጸመው የስነ ምግባር ግድፈት ከፍተኛ የጤና ችግር ሊያስከትል የሚችል ሲሆን ወይም በሰው ላይ ሞት የሚያስከትል እና ወይም በወንጀል ተጠያቂነትን የሚያስከትል ከሆነ ነው፡፡

7) በዚህ አንቀጽ መሰረት ከባድ አስተዳደራዊ እርምጃ የሚወሰደው የተፈጸመው የስነ ምግባር ግድፈት ሊያስከትል የሚችለው ጉዳት አነስተኛ ከሆነ ወይም በህይወት ወይም በጤና ላይ ምንም አይነት ጉዳት የማያስከትል ሲሆን ነው፡፡

8) ቀላል አስተዳደራዊ እርምጃ የሚያስከትል የስነ ምግባር ግድፈት በሶስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ከሁለት ጊዜ በላይ የፈጸመ ባለሙያ በከባድ አስተዳደራዊ እርምጃ ይቀጣል፡፡

## 33. <u>ቀላል አስተዳደራዊ እርምጃዎች</u>

ቀላል አስተዳደራዊ እርምጃ የሚያስቀጡ ጥፋቶች የሚከተሉት ናቸው ፡-

1) በሙያ ፈቃድ ላይ የተቀመጠውን ወሰን ወይም ተመሳሳይ ሁኔታ ተላልፎ ሲገኝ፤

2) የሙያ ስያሜን፣ ማእረግን እና ውክልናን አለአግባብ መጠቀም

3) ለፈቃድ ሰጭው አካል አስፈላጊውን መረጃ አለመስጠት፤

4) በቂ የሕክምና ምርመራን ሳያደርጉ የሕክምና ውጤትን መስጠት፤

5) ከአንድ ጤና ባለሙያ የሚጠበቀውን ሕግና ደንብ በማንኛውም ሁኔታ ሳይጠብቁ መቅረት፤

6) ስራ ላይ ሳይገኙ ሲቀሩ ለሚመለከተው የሆስፒታል አስተዳደር መረጃ ሰጥተው ፈቃድ ሳይወስዱ ሲቀሩ፤

7) ለህመምተኛው የተሰጠውን የሕክምና መረጃ በአግባቡ ሳይመዘግቡ ሲቀሩ፤

8) ሕክምናው የተከናወነው የታካሚውን ፈቃድ ሳያገኙ ከሆነ፤

9) ሌሎች ተመሳሳይ የሆኑ የስነ ምግባር መተላለፎችን ሲፈጸሙ፤

34. <u>ከባድ አስተዳደራዊ እርምጃዎች</u>

ከባድ የአስተዳደራዊ እርምጃዎች የሚወሰዱት፡-

1) ቀላል ጥፋቶችን በተደጋጋሚ ሲፈጽሙ፤

2) ለኮሚቴ የምርመራ ሂደት ትብብር አለማድረግ፤

3) በሙያዊ እንቅስቀሴ ላይ ሀቀኝነት ሲጎድል እና የማታለል ስራ ሲፈጽሙ፤

4) በሽተኞችን ሲያመናጭቁ፤

5) አልኮል ወይም አደንአዛዥ እጽ ተጠቅሞ የሕክምና አገልግሎት መስጠት፤

6) ለጤና አገልግሎት ተጠቃሚው አስፈላጊ ያልሆነ ሕክምና ማዘዝ ወይም መተግበር፤

7) የበሽተኛውን መረጃ ያለበሽተኛው ወይም ተወካዩ ፈቃድ ለሁለተኛ ወገን አሳልፎ ከሰጠ፤

8) ከበሽተኞች ጋር አላስፈላጊ የሆነ ግንኙነት (የፍቅር ወይም የጥቅም)፤

9) ወንጀል ሲፈጽሙ (የጾታ ትንኮሳ አስገድዶ መድፈር......)፤

10) በግዴለሽነት በሽተኛው ላይ አእምሮአዊ እና አካላዊ ጉዳት ሲያደርሱ፤

11) በኮሚቴው የተሰጠውን ትእዛዝና ውሳኔ በመተላለፍ ሲሰራ ከተገኘ፣ እና

12) ሌሎች ተመሳሳይ የሆኑ የስነ ምግባር ጥፋቶች ሲፈጸሙ፤

35. <u>ይግባኝ</u>

1) በፍሬ ነገር ጉዳይ ላይ ኮሚቴው የሚሰጠቀው የውሳኔ ሃሳብ የመጨረሻ ውሳኔ ይሆናል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ውሳኔ የተላለፈበት አካል በውሳኔው ላይ የሕግ ወይም የሥነ ሥርዓት ጥሰት ተፈጽሟል ብሎ ካመነ ውሳኔው በተላለፈ በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ አግባብነት ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ ማለት ይችላል፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት ይግባኝ የቀረበለት ፍርድ ቤት ይግባኙን ከተቀበለው በፍርድ ቤቱ ግኝት መሰረት ጉዳየዩ እንደገና በኮሚቴው እንዲታይ ይደረጋል፡፡

## 36. <u>ተፈፃሚነት የሌላቸው ህጎች</u>

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተመለከቱ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

## 37. <u>መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ ከዛሬ ከመጋቢት 15/2014 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**ዶ/ር ሊያ ታደሰ**

**የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጤና ሚኒስትር**